# ሕማማት በመስቀል

ከአለቃ ተገኝ ታምሩ

### ተአስሮ ድኅሬት

ርጉም ሰይጣንን ከክብሩ የሻረ
በእሳት ሰንሰለት እጅ እግሩን ያሰረ፤
እኛን ለማስለቀቅ ከሲኦል ቁራኛ
የፊጥኝ ታሰረ እንደወንጀለኛ።

### ተጸፍአ መልታህት

የሚታዘዙለት ሞገድ ማእበል
ባሕርን የሚገስጽ በነፋሳት ኃይል
ዓለምን ባንድ አፍታ መደምሰስ ሲችል
የትዕግስት መዝገብ ነውና ልዑል
በጥፊ ተመታ በሕዝብ መሐል።

### ተአርቀቀ ልብስ

በከዋክብትና ደግሞም በጨረቃ
ሰማይን አድምቆ ለብርሃን ያበቃ፤
ለመሬት ልምላሜን ሣር ቅጠል የሰጠ
ሥነ ጽጌያትን አልብሶ ያስጌጠ፤
ያዳም ካሳ ሊሆን ቀድሞ እንደ ተጻፈ
በአይሁድ አደባባይ ልብሱን ተገፈፈ።

### ተቀሰፈ ዘባን

ክፉን የሚቀሥፍ በሰይፈ እሳት
የኃያላን ጌታ የእልፍ አዕላፋት፣
እንደ ወንጀለኛ ሰርቆ እንደቀጠፈ ባደባባይ
መኻል ታስሮ ተገረፈ።

### ወሪቀ ምራቅ

የሚታዘዙለት መብረቅ ነጎድጎድ
የዓለምን ተራራች ባንድአፍታ እሚንድ፤
የሱን ውርደት ለኛ ካሳ ለማድረግ
ደበደቡት አይሁድ ራሱን በዘንግ።
ማን መታህ ንገረን አምላክ ነህ እያሉ
ተዘባበቱበት ርጉማን ሁሉ፤
በቅዱስ ምራቁ ጭቃ አርጎ ቀብቶ
የውር ዓይን ያበራው ብርሃይ አቀዳጅቶ፤
ከሃሊ ነውና ሁሉን በትእግስቱ
እርኩሳን አይሁድ ተፉበት በፊቱ።

### እክሊለ ሶክ

ዘውድን ያቀዳጀ ለነገሥታት ሁሉ
ለመሾም ለመሻር ከሃሊ በቃሉ፤
የኛር ውርደት እርሱ ተዋርዶ ሊያጠፋ
ባደባባይ መሃል የሾህ አክሊል ደፋ።

### ጸዊረ መስቀል

በመሃል እጁ ላይ ዓለም የያዘ
ለይኩን እያለ ፍጥረቱን ያዘዘ፤
ኃይላትን በሙሉ አጽንቶ ያቆመ
መስቀል ተሸክሞ በመንዝ ደከመ።

### ተቀኖዎ በቅንዋት

ብርሃን ሲጎናጸፍ ግልድም አገልድሞ
የኪሩቤል ጌታ ግንድ ተሸክሞ
ሲገፉት ሲያዳፉት ታግሶ ባርምሞ
ሦስት ጊዜ ወደቀ እንደ ፍጡር ደክሞ፤
ሐኖስን ወደ ላይ ሰቅሎ የዘረጋ
ዓለምን በቃሉ አጽንቶ ያረጋ
ባለ ግርማው ንጉሥ በለበሰው ሥጋ፤
ውርደትን ለመሻር በርሱ መዋረድ
የዘለዓለም ሞትን ከኛ ሊያስወግድ
እጅ እግሩን ቸንክረው ሰቀሉት አይሁድ።

### ስሪበ ሐሞት

የአፍላጋትና የውቅያኖስ
የቀላያት ሁሉ ፈጣሪ ንጉሥ፤
የኛን ጥም ለማርካት ተጠማሁ ስላለ
ሐሞትና ከርቤ የተቀላቀለ
ጠጣ ብለው ሰጡት እንደተሰቀለ።

### እርግዘተ ገቦ

ሁሉ ተፈጸመ ብሎ በአንደበቱ
ነፍሱን በገዛ እጁ ሰጠና ላባቱ
አንገቱ ዘፍ አለ በጊዜ ተሰዓቱ፤
ቀዳሚ ድኅረ አልፋና አሜጋ
ተዋህዷልና ሰብአዊ ሥጋ
ፍጹም ንፁሕ ሥጋው ከመስቀል ቢጠጋ
በአንድ ሐራዊ ጦር ጎኑ ላይ ተወጋ
የሕይወትን ውኃ ሊሰጠን በጸጋ።

### ወሪደ መቃብር

ያልተወሰነለት መጠንና ልክ
ዓለም የማትበቃው የባህርይ አምላክ፤
በዮሴፍና በኒቆዲሞስ
ተገንዞ በክብር በድርብ ነጭ ልብስ፤
ምድረ ጎልጎታ ወደተባለችው
ሦስት ክንድ ተኩል መሬት ወሰነችው።

እሱ ተበድሎ እሱ እንደመበቀል
፲፫ቱን ሁሉ ህማማተ መስቀል፤
ለተቀበለልን የአርያም ጌታ
እራሱ ለካሰው በበደልነው ፈንታ
እጹብ ድንቅ እጹብ ድንብ ብለን ጠዋትማታ
ከማመስገን በቀር የለውም ወሮታ፤
በሞቱ ሊያድነን ወርዶ ሰው የሆነው
ያስገደደው የለም በፈቃዱ እንጂ ነው።